የሰ/መ/ቁ. 18809

ሰኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን እቁበዮናስ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ሚሊዮን ዑመር - ጠበቃ አዳሙ ደነቀው - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- የፌደራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን ነገረ ፈጅ ገ/እዛቤር ሙላቸውና ተፈራ ጥላው ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለውሳኔ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 15697 ህዳር 30 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች ተጠሪው ያለአግባብ ከግብር ህግ በተለይም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ካወጣው ደንብ ቁጥር 75/1993 ውጭ የትራንስፖርት መኪና ለመንገድ ስራ ድርጅት በማከራየቴ ብቻ የሰበሰውን ገንዘብ እንዲመልስ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበው ክስ፣ ሲሆን ተጠሪው በበኩሉ ግብሩ የተሰበሰበው በደንብ ቁጥር 75/1993 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 9 መሰረት ስለሆነ፣ገንዘቡ መመልስ የለበትም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካች ገንዘብ እንዲመለስ የወሰነ ሲሆን፣ በዚህ ውሣኔ ተጠሪው ቅር በመሰኘት ይግባኝ አቅርቦ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮታል፡፡



አመልካች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሳሳተ የሕግ ትርጓሜ ሰጥቷል፡፡ ያከራየነው መኪና እንጅ መሣሪያ ባለመሆኑ ደንብ ቁጥር 75/1993 በእኛ ላይ ተፈፃሚነት የለውም በማለት የተከራከረ ሲሆን ተጠሪው በበኩሉ፣ ግብሩ በአግባቡ ነው የተሰበሰበው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመረነው "ኮምፒውተርን ጨምሮ ከተለያዩ መሣሪያዎች ህንፃዎች እና ሌሎች እቃዎች ኪራይ" አምስት ፐርሰንት ግብር እንደሚከፈል፡፡ ደንብ ቁጥር 75/1993 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 9 ይደነግጋል፡፡

አመልካች "መሣሪያዎች" የሚለው የትራንስፖርት መኪናን አይጨምርም የሚል ክርክር ያቀረበ ቢሆንም መኪኖቹ ለህዝብ ማመላለሻ እና ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠታቸው ቀሞ በኪራይ ለኮንስትራክሽን ድርጅቱ በመከራየታቸው በደንቡ የተመለከተውን ግብር ከመክፈል ነፃ የሚሆኑበት ሁኔታ የለም፡፡ የህግ አውጭው ሐሳብም የህዝብ ማመላለሻ መኪና ከመደበኛው ስምሪት ወጥቶ ከተከራየ ከኪራዩ ግብር ለማስከፈል እንደሆነ ከደንብ ቁጥር 75/1993 ድንጋጌዎችና ይህንን ደንብ ለማሻሻል ከወጣው ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 2/ሸ/ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ፍሬ ያለው ሆኖ ስላላገኘው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ውሣኔውን በማጽናት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ይፃፍ፡፡
3. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



# የ ን ግ ድ
# ተ ቋ ማ ት